# አትሰቀል ይቅር!

(አሥራደው ከፈረንሳይ)



በገባለት ቃሉ: አባትህ ለ'ኛ አባት፤
አንተ ለኛ ሞተህ: ልንድን ከሃጢያት፤
እኛን አድናለሁ: ብለህ ከመከራ፤
መስቀል ተሸክመህ: አትውጣ ተራራ::
በጨካኞች ጅራፍ: አይገረፍ ጀርባህ፤
ምስማር አይቸንከር: በጅና በግሮችህ፤
በጦር አይወጋ: አይበሳ ጎንህ፤
አትጠጣ ፍጹም: የሃሞት መራራ፤
አድናለሁ ብለህ: እኛን ከመከራ፤
መከራህ አይብዛ: መከራችን ላይቀር፤
ተንገላተህ አትሙት: አትሰቀል! ይቅር::

ተከባብሮ መኖር: አብሮ መብላት ቀርቶ፤
ጥላቻ፤ ጭካኔ፤ መከራ በርክቶ፤
ወንድማማችነት፤ ፍቅር መተባበር፤
አንድነት፤ ነፃነት፤ ፍጹም ጠፍተው ካገር፤
መቻቻል፤ ደግነት፤ ከሃገር ተሰደው፤
ግፍ በደል በርክቶ: ሞልቶ ፈሶ ጽዋው፤
ሰው ሆነን ሰው ካልሆን: ተፈጥረን ባምሳልህ፤
ከሰማየ ሰማይ: ወርደህ ከዙፋንህ ፤
አፈር ለባሽ ገላ: ከንቱ ሥጋ ለብሰህ፤
አትሰቀል በቃ! እኛን ላድን ብለህ ::

ይልቅስ ከሰሙህ እንዲህ ምከራቸው.........!
እንደዚህ በላቸው.... !

ሰልጣን ተገን አርጎ: ቀምቶ የበላ፤
ለሥጋው አድልቶ: ወገኑን ያጉላላ፤
ዘረኝነት አርሶ: ቂም በቀል የዘራ፤
የሚያበዛ ትʼቢት: ሰው የሚያስፈራራ፤
ውሸት ያመረተ: በደል የከመረ፤
በግፍ የገደለ: ወህኒ ቤት ያጎረ፤
ጥላቻን አንግሶ: ፍቅርን ያኮሰሰ፤
ወንድሙን የገፋ: በደል ያነገሰ፤
ቁጣዬን አብዝቶ: መከራውን ያጭዳል፤
ሕዝቤን አታጉላሉ: ከንግዲህ ይበቃል !
ብለህ ንገራቸው.........!
ሰልጣን ላዋሰካቸው......... !
ልቦና ቢገዙ.... ድንገት ቢመለሱ.... ወደ ሕሊናቸው ::

ግን፤

የሕዝብህን ጩኸት: እየሰማ ጆሮህ፤
ሰቃይ መከራውን: እያየኸው ባʼይንህ
ሲካድ ሰብዕናው: ፈጥረኸው ባምሳልህ፤
ዝምታህ ከበዛ: ከዘገየ ፍርድህ፤
ላማ ሰበቅታኒ: ኤሎሄ ! ኤሎሄ ! ላʼባትህ ልናገር፤
ቁም ሰቅልህ ይብቃ! እኛ አልዳንምና: አትሰቀል ይቅር!!

ሚያዝያ 4 ቀን 2004 ዓ.ም. (April 12/2012)

በሰደት ለሚጉላሉ፤ ለተገፉ ሕዝቦችና፤ ለተጨቆኑ ነብሶች ነፃነት፤ ማስታወሻ የተቋጨች::



EthioLion.Com